## ትምህርት አንድ

## የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያ

- ***መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው/ የቃሉ አመጣጥ ከወዴትና ምንስ ያመለክታል?***

መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉ እንደሚያመለክተው መጽሐፍ እና ቅዱስ የሚሉ የሁለት ቃላት ጥምረት ነው። በግሪክ ቋንቋ ቢብሎስ (byblos) ከደንገል በተሠራ ወረቀት ወይም በብራና ከተጻፈ በኋላ በሁለት በትሮች የሚጠቀለል መጽሐፍ ያመለክታል። ቢብሎስ በእንግሊዝኛው ባይብል ተብሎ ሲተረጎም በአማርኛው ደግሞ መጽሐፍ በሚለው ቃል ተተረጎመ። የግሪኩ ቃል ቢብሎስ (byblos) እራሱ ቢብሎሰ (byblos) ከተባለ ከተማ ስም የተገኘ ነው፤ እርሱም ከኒቂያ ወደቦች መካከል በቤይሩት 25 ማይል ያህል የሚገኝ አገር ነው።ለመጽሐፍ ያገለግል ዘንድ ፓፒረስ (ደንገል) የተባለውን ተክል እንደ ወረቀት አድርገው ይሠሩበት የነበረ ቦታ ነው።

ሁለተኛው ተጨማሪ ቃል ቅዱስ የሚለው ሆነ ትርጓሜውም የተለየ ማለት ነው። ሰው ወይም ማንኛውም ነገር ለእግዚአብሔር ሲለይ ቅዱስ ይባላል። ሰዎች (ዘጸ. 28፡41) እንስሳ (ዘጸ. 13፡2) ቦታዎች (ዘጸ. 3፡5) ቀኖች (ዘፍ. 2፡3) ማናቸውም ነገር ቅዱስ ሊባል ይችላል (ኢያሱ 6፡19)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥምረት ወደሆነው ቅዱስ ወደሚለው ቃል ስንመጣ ደግሞ ይህ መጽሐፍ እንደማንኛውም ተራ መጽሐፍ የሚታይ ሳይሆን የተቀደሰና የተለየ መሆኑን ከማሳየትም አልፎ የጻፉት ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተውና ተመርተው እንደነበር ያስገነዝባል። በእርግጥም የጻፉት ሰዎች ከራሳቸው ልቡና ፈጥረው ወይም አንቅተው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት በእግዚአብሔር እየተመሩና እየታዘዙ የጻፉት ነው (ዮሐ. 14፡26)።

ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ህልውናውንና ፈቃዱን ረቂቅ ባሕሪውን በተወሰነ መልኩ የምንረዳበትና ፈቃዱንም ምን እንደሆነ ማወቅ የምንችልበት በእግዚአብሔር በራሱ መንፈስ መሪነት የተጻፈና ለሰው ልጆች የተሰጠ (የተገለጠ) ቅዱስ ቃል ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ እንደሚለው ከመጀመሪያው ስለነበረው ስለ ሕይወት ቃል እንድንጽፍላችኊለን፤ ይህ የሕይወት ቃል የሰማነውንና በዓይኖቻችን ያየነው የተመለከትነውና በእጆቻችን የዳሰስነው ነው። ይህ ሕይወት ተገልጦአል፤ እኛም አይተነዋል፤ እንመሰክራለንም። በአብ ዘንድ የነበረውንና ለእኛም የተገለጠውን የዘለዓለም ሕይወትእንነግራችኊለን። ኅብረታችንም ከአብ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው። ደስታችንም ሙሉ እንዲሆን ይህንን እንጽፍላችኊለን (ዮሐ. 1፡1-4)።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ "ዘለዓለማዊ ሕግ" ሲሆን ዓላማውም ሰዎችን ለሰማያዊ መንግሥት ማብቃት ነው። ስለዚህ ከሌሎች የሳይንስ፤ የልቦወለድና የፍልስፍና መጽሐፍ ፈጽሞ ይለያል።

ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ከመጻፉ አልፎ የሚያነቡትና የሚሰሙትን የሚመክር፣ የሚገስጽ፣ የሚያረጋጋና ወደ ደኅንነት ሊያደርስ የሚችል ጥበብ ያለው በመሆኑ ነው (2ጢሞ. 3፡14-17፤ ሐዋ. 13፡16)። ከዚህም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ ጣፋጭ የሆነ የሚበላ ሰማያዊ ስንቅ (ሕዝ. 3፡1-3)፣ ብርሃን ሆኖ የሚመራ (መዝ. 119፡105)፣ አጽናኝና መካሪ መሆኑን በተለያዩ ቦታዎች ተገልጾ ይገኛል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተገኘና እርሱ በመረጣቸው ቅዱሳን ሰዎች በራሱ መንፈስ መሪነት የተጻፈና ከሰው ልጅም ጋር ቃል ኪዳን ያጸናበት ቅዱስ ቃል ነው።

በጥንት ዘመን ግን እስከ (100 ዓ. ም.) ድረስ የቅጠል ዓይነት መጽሐፍ፣ አሁን ያለው ዓይነት ስላልነበር መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ቃል ጥቅልል በሚል ስም ይታወቅ ነበር። የጥቅልል ርዝመት ዐሥር ሜትር ሊደርስ ይችል ነበር። ጽሕፈቱም በዐምዶች ላይ ነበር (ኢሳ. 33፡4፤ ኤር. 36፡2፤ ሕዝ. 3፡1-3፤ ሉቃ. 4፡17-19፤ 2ዮሐ. 1፡2፤ ራእ. 5፡3)። በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዘመን በወረቀት ወይም በብራና የተጻፈውን ሲያመለክት የጥቅልል መጽሐፍ እንጂ በቅጠል ላይ የተጻፈ መጽሐፍ አልነበረም። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳት መጻሕፍት መዝገብ ነው። ብሉይ ኪዳን ከ1300-400 ከክ.ል.በ በልዩ ልዩ ቦታዎች አርባ በሚያህሉ ጸሐፊዎች እንደተጻፈ ይነገራል። አዲስ ኪዳን ከ45-96 ዓ. ም. በስምንት ሰዎች ተጻፈ። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር በራሱ መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው ተብሏል።

**መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የእግዚአብሔር መንፈስ ለምን አስፈለገ?**

የእግዚአብሔር መንፈስ ካስፈለገባቸው ጥቂት ምክንያቶች መለጥቀስ ያህል።

- የሰው ልጅ አስቦ ሊደርስባቸው የማይችላቸው እጅግ በጣም ጥልቅና ረቂቅ የሆኑ ነገሮችን የያዘ መጽሐፍ በመሆኑ፤
- ያለስህተትና ምንም ዓይነት ልዩነት ሳያንጸባርቅ እንዲጻፍ (የዘር፣ የቀለም የጎሣ፣ የጾታ)
- አንድ ዓይነት የሆነ የሃይማኖት የሥነ ምግባር ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ፤
- እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች እንዲጻፉና የማይፈልጋቸው ጉዳዮች እንዳይጻፉ ለማድረግ፤ ይህም ማለት በመንፈሱ በመመራት ትክክለኛውን ቃሉ መጻፍ እንዲቻል፤
- የሰው እውቀትና ችሎታ እጅግ በጣም የተወሰነና የተገደበ ነው፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ምሥጢራዊ ከሰው አእምሮና ጠቅላላ ችሎታ በላይ ስለሆነ ይህንን ቃል ለመጻፍ የእግዚአብሔርን መንፈስ ድጋፍ እጅግ በጣም ያስፈልግ ነበር።
- ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር "እኛ ግን እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካይነት ምሥጢሩን ገልጦልናል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንፈስ ጥልቅ የሆነውን ዕቅድ እንኳ ሳይቀር ሁሉ ነገር ይመረምራል። ስለ ሰው የሐነ እንደሆነ ከገዛ ራሱ መንፈስ በቀር በእርሱ ያለውን አሳብ የሚያውቅ ሌላ ማንም የለም፤ እንዲሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር የእግዚአብሔር አሳብ

የሚያውቅ ማንም የለም" (1ቆሮ. 2፡10-11)። ስለዚህ እግዚአብሔር የተናገረውን ተረድቶ ለመጻፍ የራሱ መንፈስ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

**ቅዱሳን መጽሐፍ የተጻፉት በምን ዓይነት መልኩ ነው ይህን የእግዚአብሔር ቃል የተቀበሉት እንዴት ነው ይህ ቃል ወደ እነርሱ ሊመጣና ሊጽፉት የቻሉት በምን ዓይነት መልክ ነው እግዚአብሔር ቃሉ ወደ እነርሱ እንዲደርስ ያደረገው?**

እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ቃሉን ወደ ሚያደምጡት ቅዱሳኖች አስተላልፏል። ቃሉ ለእነርሱ ከመግለጹ በፊት ግን በጎ ፈቃደኝነት ይጠይቃል። ማንም ሰው በእግዚአብሔር ተገዶና ነጻነቱ ተነፍጎ አይደልም የሚፈጽመው። ጸሐፊው በበጎ ፈቃደኝነት በነጻነት ራሱን ያዘጋጃል፤ ከዚያም እግዚአብሔር የገለጸለትን ቃል በራሱ ቋንቋ፣ ባሕልና የአጻጻፍ ዘይቤ መሠረት ቃሉን ይጽፋል። እግዚአብሔር ቃሉን በሚከተሉት መንገዶች ለጸሐፊዎች ይገልጻል፡-

- ✓ ቃል በቃል በማነጋገር፡- ሙሴን እንዳነጋገረው እግዚአብሔር ቃሉን በንግግር መልክ ይገልጻል። ለምሳሌ፡- "በድንገት እግዚአብሔር ሙሴን፣ አሮንና ሚርያምን እናንተ ሦስታችሁ እኔ ወደ ምመለክበት ድንኳን ደጃፍ ኑ አላቸው፤ እነርሱም ሄዱ፤ እግዚአብሔርም በደመና ዐምድ ወርዶ በድንኳኑ ደጃፍ በመቆም አሮን ሚርያም ብሎ ጠራቸው፤ ሁለቱም ወደ ፊት ቀረቡ፤ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፤ እነሆ እኔ የምነግራችሁ አድምጡ . . እኔ ከእነርሱ ጋር ቃል በቃል በግልጥ እነጋገራለሁ" (ዘኁ. 12፡48)
- ✓ በሕልም በመግለጽ (ዘፍ. 37፡5)።
- ✓ በትንቢትና በራእይ ራሱን በመግለጥ፤ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፤ "እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ" (ዘኁ. 12፡6)፤ የምታየው በመጽሐፍ ጽሑፍ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ላክ አለኝ።
- ✓ ያዩትንና የሰሙትን ልብ ብለው፣ አስተውለው ያንኑ እውነታ ብቻ እንዲጽፉ በማድረግ፤ ቅዱስ ዮሐንስ እንደጻፈው "ገና የምነግራችሁ ብዙ ነገር አለኝ፤ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ ምክንያቱም እርሱ የሚናገረው የሰማውን እንጂ የራሱን አይደለም። እርሱ ወደፊት የሚሆኑትን ነገሮች ይነግራችኋል" (ዮሐ. 16፡12)።

**መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዋና ዓላማ ምንድን ነው?**

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉባቸው ዓላማዎች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ በጥቂቱ

- የእግዚአብሔር ማንነት ለማወቅና ለመረዳት እንዲሁም እውነተኛና ዘለዓለማዊ አምላክ መሆኑን ተገንዝበን እንድናመልከውና ፈቃዱንም ፈጽመን በሕይወት እንድንኖር (1ዮሐ. 1፡1-4፤ ማቴ. 28፡20፤ ሮሜ. 15፡4)።

- ሥጋን ለብሶ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ጌ.ኢ.ክ እግዚአብሔር እንደሆነ አምነን በስሙም ዘለዓለማዊ ሕይወትን እንድናገኝ (ዮሐ. 20፡30-31፤ 1ዮሐ. 5፡13)።
- "እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማና በላከኝም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው" (ዮሐ. 5፡24)። እንዳለው በእግዚአብሔር ና በልጁ በጌ.ኢ.ክ አምነን የዘለዓለም ሕይወት እንድንወርስ።
- የሰው ልጅ በጥሩ ሥነ ምግባር ማደግ ወይም መታነጽ እንዲችል የተጻፈ ነው። የሰው ልጅ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ሥነ ምግባራት በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ተገልጸዋል (ዘጸ. 20፡7-17፤ ማቴ. 5፡21)። በአጠቃላይ የሰዎች ሥነ ምግባር ጥሩ መሆን ብቻ ሳይሆን ከክፉት መራቅና ፈተናን ማለፍ የሚችለው በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው እግዚአብሔርን በማወቅና እርሱን በመፍራት ላይ ሲመሠረት።

**መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ መጻሕፍት መዝገብ ወይም ስብስብ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን እንዴት አድርጋ ነው እነዚህ መጻሕፍት ሁሉ አግኝታ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ የሰበሰበቻቸው?**

- ከመጀመሪያ ጀምሮ ቤ/ክ አይሁድ ያወቁአቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተቀበለች። ቀጥላም በሐዋርያት ወይም በሐዋርያት ሥልጣን የተጻፉትን መጻሕፍት ሰብስባ እንደ እግዚአብሔር ቃል ተቀበለቻቸው። የቤ/ክ አባቶች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እየጠቀሱ አስተማሩ። ቅዱስ አትናቴዎስ በ367 ዓ. ም. በጻፈው በፋሲካ ዕለት ቃለ በረከት ለመጀመሪያ ጊዜ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሃያ ሰባት (27) ብቻ መሆናቸውን ተናገሯል። እንደዚሁም በ397 ዓ. ም. በሰሜን አፍሪካ በካርታጎ (በካርቴጅ በቱኒዚያ) የተደረገው ሲኖዶስ ሃያ ሰባቱን መጻሕፍት አጸደቀ።
- በሌላ መልኩ በዕብራይስጥ የተጻፉ ብዙ የብሉይ ኪዳን ቅጂዎች የነበሩ ቢሆንም የመጀመሪያው ቅጂ በ200 ከክ.ል.በ ገደማ ተጻፈ። ቅዱሳት መጻሕፍት በጥንት ዘመን በጥቅልል እየተጻፉ በልዩ ልዩ ምኩራብና ቤ/ክ ይሰበሰቡና ይነበቡ ነበር። ቅደም ተከተላቸውም ልዩ ልዩ ነበር። ለምሳሌ አትናቴዎስ ሰባቱን መልእክታት ከጳውሎስ መልእክታት አስቀድሟል። የካርታጎ ሲኖዶስ ግን የመጻሕፍቱን ተራ እንደ አሁኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ተራ አደርጎ አጽድቋል።

➢ **የቅዱሳት መጽሐፍት ቀኖና ማለት ምን ማለት ነው? ቤ/ክ የቅዱሳት መጻሕፍት ብዛትና ይዘት ተቀብላ ከማጽደቋ ጋር ምን ግንኙነት አለው?**

- "ቀኖና" የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም መቃ ወይም መለኪያ ሸምበቆ ማለት ነው። ቀኖና የሚለው ቃል በጥንት ዘመን የታሪክ ሰዎች ጥሩ ቁመና ላለው ሰው ወይም ቀጥ ላለ ነገር ይጠቀሙበት ነበር። የቤ/ክ ቀኖና ሲባል የቤ/ክ ሕግ ወይም ትክክለኛ (ቀጥተኛ) እምነት ማለት ነው።

- የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና ሲባል ቤ/ክ የሃይማኖትን ትምህርት ለመግለጥና ለማስተማር በማለት የተለያዩ መሥፈርቶች በመጠቀም ቅዱሳት መጽሐፍትን ይዘታቸው በደንብ አድርጋ አጥንታና መርምራ በጉባዔ (ሲኖዶስ) አቅርባ የምትወስንበት ሂደት ነው፡፡ ይህም ማለት የመጽሐፍቶቹን ይዘት አብጠርጥራ ካየች በኋላ ቅዱሳት መጽሐፍትን በብዛታቸውና በአቀማመጣቸው ወስና የምታጸድቅበት ሂደት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የማቴዎስ ወንጌልን እንውሰድ፤ ቤ/ክ ይህን መጽሐፍ አንብባ ይዘቱን በደንብ ከተረዳች በኋላ በቅዱሳት መጽሐፍ ውስጥ አካተተችው፤ የቶማስ ወንጌል የተባለውን ግን አላካተተችውም፤ ምክንያቱም በቅዱሳት መጽሐፍት ቀኖና (ካኖን) ሕግ መሠረት መሠረት ያላሟላቸው ነገሮች ስላሉ ነው፡፡ ቤ/ክ የቅዱሳት መጽሐፍትን ቀኖና ተጠቅማ መወሰን የፈለገችበት ሌላው ምክንያት በሐዋርያቶችና በቅዱሳን ስም የተለያዩ የሐሰት መጻሕፍቶች እየተበራከቱ ስለመጡ እውነተኞቹ በሐዋርያትና በቅዱሳን አባቶች የተጻፉትን መጻሕፍቶች ለይቶ ለማስቀመጥ በማሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቅዱስ ጳውሎስ ከሞተ በኋላ አንዳንድ ሰዎች እሱ ያልጻፈውን እራሳቸው በመጻፍ ይህ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ነው እያሉ በመምጣታቸው ቤ/ክ ትክክለኞቹን የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች መለየትና በቀኖናዋ ማካተት ጀመረች፡፡
- ቀኖናዊ ሆነው የሚቆጠሩትን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ለመወሰን የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትሲኖዶስ ተቀምጠው የየራሳቸው ውሳኔዎች ወስነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በቁጥር ብዛቱ አንድ ወጥ የሆነ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ያለው መጽሐፍ እንዳይኖር አድርጓል፡፡ በእርግጥ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የየራሳቸው መሥፈርቶች በመጠቀም ስለወሰኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር ላይ ልዩነት ሊፈጥር ቻለ፡፡ ለምሳሌ፡- ካቶሊካዊት ቤ/ክ 73 መጽሐፍት ስትቀበል ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ 81 እና የፕሮቴስታንት ደግሞ 66 በመሆን ልዩነት ፈጥሯል፡፡

**ከመቼ ጀምሮ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፍና በቁጥር ተከፋፍሎ መነበብ የጀመረው?**

- መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ የጻፉት ሰዎች በክፍል፣ በምዕራፍና በቁጥር አለዩትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፎች የተከፈለው በ1228 ዓ. ም. በእንግሊዝ ሀገር ሲሆን ምዕራፎቹ ደግሞ በቁጥር የተከፈሉት በ1543 ዓ. ም. በፈረንሳይ ሀገር ነው፡፡ አከፋፈሉ እስካሁን ድረስ ይሠራበታል፡፡

➢ **መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በምን ቋንቋ ነው የተጻፈው? አዲስ ኪዳንና ብሉይ ኪዳን በመባል የመከፈሉ ምክንያትስ ምንድን ነው?**

- መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አካትቶ የያዘ ሲሆን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከክርስቶስ በፊት የተጻፉ፣ እስራኤል የተቀበሉአቸው፣ በክርስቶስም የጸደቁ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲሆኑ የተጻፉትም በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው፡፡ በዕብራይስጥ ቋንቋ

የተጻፈው ብሉይ ኪዳን ከጌታችን ልደት በፊት ወደ ግሪክ ቋንቋ ተተርጉሞ ነበር፤ ትርጉሙም ሴፕቱአጂንት (የሰባ ሊቃናት ትርጉም) ተብሎ ይጠራል። አልፎ አልፎ በጥቂቱም ቢሆን አራማይስጥ በውስጣቸው ያካተቱ እንደ ትንቢተ ዳንኤል ዐይነቶች ይገኛሉ።

- አዲስ ኪዳን ግን በብሉይ ኪዳን የተተነበየ (ኤር. 31፡31-34) እና ክርስቶስ ደሙን አፍስሶ ያቆመው ቃል ኪዳን ነው (ሉቃ. 22፡19-20)። በሐዋርያት ሥልጣን የተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት አዲሱን ኪዳን ስለሚገልጡ አዲስ ኪዳን ተብለዋል። አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ፍጹም አድርጎታል፤ በአሮጌውም ፈንታ አዲሱ ተተክቷል (ዕብ. 8፡13)። የተጻፈውም በግሪክ (በጽርእ) ቋንቋ ነው። በእርግጥ አዲስ ኪዳን በድንጋይ ላይ ሳይሆን በልብ፣ በቀለም ሳይሆን በመንፈስ ተጻፈ፤ የኩነኔ ሳይሆን የጽድቅ አገልግሎት አለው፤ ለጊዜው ሳይሆን ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል። ስለዚህ ክብሩ ከፍ ያለ ነው (2ቆሮ. 3፡4-18)።

## መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሀገራችን ቋንቋዎች (ግእዝና አማርኛ) መቼና በማን ተተረጎመ?

- በኢትዮጵያ በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጡ ተሰዐቱ ቅዱሳን (ዘጠኙ ቅዱሳን) ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ እንዲተረጎሙ አደረጉ። ከእነርሱ ዘመን ቀደም ብሎ አንዳንድ መጻሕፍት በእነ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ጥረት በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተተርጉመዋል። በ1548-1549 አባ ተስፋጽዮን የተባሉ ከአንድ የመነኮሳት ቡድን ጋር በመሆን በቫቲካን ግቢ (ሮማ) ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ ኪዳንን አሳተሙ (ለሕትመት አበቁ)። እነዚህ መነኮሳቶች የአህመድ ግራኝን ወረራ በመሸሽ በሮም ተጠልለው እንደነበር ይታወቃል።
- መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ በነጠላ ትርጓሜ ወደ አማርኛ የተረጎመ አብርሃም (አባ ሮሜ) የሚባል መነኩሴ ነበር። ይህም ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በኩል በ1816 ዓ. ም. አራቱ ወንጌላት፣ በ1821 ዓ. ም. አዲስ ኪዳን፣ በ1832 ዓ. ም. ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞ ወጣ። የዕብራይስጥንና የግሪክን ቋንቋ የሚያውቁ አንዳንድ የውጭ አገር ዜጎች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር ትርጉሙን ካሻሻሉት በኋላ በ1878 ዓ. ም. እንደገና ታርሞ ታተመ፤ ከዚያም ወዲህ በየጊዜው ታትሞ ወጥቷል።
- ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ የቀድሞው ትርጉም እንዲታረም ስለታሰበ ብዙ ሊቃውንት ከደከሙበት በኋላ በ1953 ዓ. ም. አዲሱ ትርጉም ታተመ። ከዚያም በኋላ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ቀለል ባለ አማርኛ በ1980 ዓ. ም. አዲስ ትርጉም አሳተመ።

**የትምህርቱ ዋና አዘጋጅ፡- አባ ምሥራቅ ጥዩ**

**የትምህርቱ አስተባባሪ፡- አቶ ተስፋዬ ባደገ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመለሱ በኋላ ወደ ሀገረስብከቱ የተልእኮ ትምህርት ዝግጅት ክፍል ይላኩት።

**የተማሪው/ዋ ስም ----------------------------------ኮድ-------- ቁምስና--------------------ውጤት---------**

1. ከሚከተሉት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የእግዚአብሔር መንፈስ ካስፈለገባቸው ምክንያቶች ውስጥ የማይመደበው (የሌለው) የትኛው ነው? ሀ) ያለ ስሕተትና ምንም ዓይነት ልዩነት ሳያንጸባርቅ እንዲጻፍ ለ) እግዚአብሔር የተናገረውን ተረድቶ ለመጻፍ ሐ) የእግዚአብሔር ቃል ምሥጢራዊ፣ ከሰው አእምሮና ጠቅላላ ችሎታ በላይ ስለሆነ መ) ሰው አመፀኛ ስለሆነ
2. መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በምን ቋንቋ ተጻፈ? ሀ) ብሉይ ኪዳን በግሪክ አዲስ ኪዳን በአራማይስጥ ለ) ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ አዲስ ኪዳን በአራማይስጥ ሐ) ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ አዲስ ኪዳን በግሪክ መ) ብሉይ ኪዳን በግሪክ አዲስ ኪዳን በዕብራይስጥ
3. ቤ/ክ የሃይማኖትን ትምህርት ለመግለጥና ለማስተማር በማለት የተለያዩ መሥፈርቶች በመጠቀም ቅዱሳት መጽሐፍትን ይዘታቸውን በደንብ አድርጋ አጥንታና መርምራ በጉባዔ (በሲኖዶስ) አቅርባ የምትወስንበት ሂደት ምን በመባል ይታወቃል?
4. መጽሐፍቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት የሚለይበት ዋናው ምክንያት ምንድን ነው?
5. እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ቃሉን ወደ ሚያደምጡት ቅዱሳኖች አስተላልፏል። ቅዱሳኖችም ይህንን ቃል በጽሑፍ አስፍረውታል። እግዚአብሔር ቃሉን ወደ ሚያደምጡት ቅዱሳኖች መልእክቱን ለማስተላለፍ ከተጠቀመባቸው መንገዶች ውስጥ ሕልምና ራእይ ይገኙበታል። ለመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አኳያ ሕልምና ራእይ ልዩነታቸው ምንድን ነው?
6. ሰዎች በዕለታዊ ሕይወታቸው ውስጥ አለመተማመን ሲጠፋ ወደ መማማል ይደርሳሉ፤ በአንዳንድ ቦታዎች በተለይም በፍርድ ቤቶች ውስጥ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ሲምሉ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ሲያስምሉ ይታያል። ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ መማል ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ማስማል ምን ትርጉም አለው? ለምንስ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ይምላሉ?